ቀን 8/8/2000

**ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**ቀጥታ ክስ ችሎት**
**አዲስ አበባ**

**አመልካች፡-** መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም አራቱም ፓርቲዎች በውህደት ያቋቋሙት ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር (በተወካያቸው በአቶ አባይነህ ብርሃኑ አማካኝነት)

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ

## በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 46/86 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 25 (1) መሠረት የቀረበ አቤቱታ

- ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን ተቀብሎ ለማየት የዳኝነት ሥልጣን አለው
- አመልካችና ተጠሪ በሕግ ችሎታ አላቸው
- አመልካች የሚከራከረው በፓርቲው ሊቀመንበር ተወካይ አማካይነት ነው
- የአቤቱታ ማቅረቢያው ይርጋ ጊዜ አላለፈም
- የፍርድ ቤቱን መጥሪያ በተጠሪ አድራሻ መስጠት ይቻላል

## 1. የአቤቱታ ዝርዝር

1.1. አራቱ የፖለቲካ ድርጅቶች መስከረም 14 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረጉት ውህደት መሠረት ‹‹ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ›› የሚል አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ተቋቁሟል፡፡ ይኸው አገር አቀፍ ፓርቲ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 46/86 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 22 መሠረት ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ጥቅምት 18 ቀን 1998 ከተጻፈ ማመልከቻ ጋር የውህደቱን ሰነዶች በማያያዝ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡

1.2. ቦርዱ ጥያቄውን ተቀብሎ በአዋጁ አንቀጽ 24 መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ሲገባው የቀረበው የምዝገባ ጥያቄ አሁን ባለበት ሁኔታ የተሟላ ባለመሆኑ ለቦርድ አይቀርብም ተብሎ በጽ/ቤቱ ም/ዋና ኃላፊ መልስ የተሰጠ ሲሆን ይህ የም/ዋና ኃላፊው መልስ